Rift Valley Institute
MAKING LOCAL KNOWLEDGE WORK

Peace Research Facility

# የሴቶች ሚና በኢትዮጵያ ክልላዊ እና አገር አቀፍ የሰላም ሂደቶች

ገሊላ ታፈሰወርቅ

ጥቅምት 2016

በኢትዮጵያ ውስጥ ያሉ ሴቶች የተለያዩ የፖለቲካ፣ የጸጥታ፣ የኢኮኖሚ እና የማኅበራዊ ተግዳሮቶች ያጋጥሟቸዋል። በሌሎች አገሮች እንደሚታየው ሁሉ፣ በኢትዮጵያ የሚከሰቱ ግጭቶች ሴቶችን ተመጣጣኝ ላልሆኑ ስቃዮች፥ ጥቃቶችና እና የሰብአዊ መብት ጥሰቶች ያጋልጧቸዋል። ይህም የሰላምን አስፈላጊነት የሚያጎላ ሲሆን፣ የሴቶችን እና የልጃገረዶችን ደኅንነት ከማረጋገጥ ባለፈ የሴቶችን መብት ከማክበር ጋር የተያያዘ ነው። ከዚህ ጎን ለጎን የሰላም ሂደቶችን ዘላቂነት እና ህጋዊነት ለማረጋገጥ ትርጉም ያለው የሴቶች ተሳትፎ ወሳኝ ነው። በአሁኑ ጊዜ ግን ሴቶች በተለያዩ ደረጃዎች ሙሉ ብቃት ያላቸው ሰላም ፈጣሪዎች መሆናቸውን በተደጋጋሚ ቢያሳዩም ለሰላም መስፈን የሚያበረክቱት አስተዋፅኦ እጅግ በጣም አነስተኛ ነው። ይህ ጽሑፍ የኢትዮጵያ አገራዊ የምክክር ኮሚሽንን እና የቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል የሰላም ሂደቶችን በምሳሌነት በመጠቀም በእነዚህ ሁለት ሂደቶች ውስጥ የሴቶች መካተት እስካሁን በታዩት ውጤቶች ላይ እንዴት ከፍተኛ ተጽዕኖ እንዳሳደረ ያሳያል።

# የአገራዊ ምክክር ሒደት

በ2010 (እ.ኤ.አ. በ2018) ኢትዮጵያ በተለያዩ ትርጉም ያለው የፖለቲካ ለውጥ እና ውክልናን በሚጠይቁ ሕዝባዊ ፀረ-መንግሥት ተቃውሞዎች ተናውጣ ነበር። የተቃውሞ ሰልፎቹ በመጨረሻ የታጠቁ ኃይሎች ትጥቅ ፈትተው ሰላማዊ የፖለቲካ ተሳትፎ እንዲያደርጉ እንዲሁም ብጥብጥ መቀስቀስ የቀጠሉትን የተለያዩ ነባር ቅሬታዎችን ለመፍታት እንዲቻል ጥሪዎች እንዲቀርቡ አድርገዋል። ይህንንም ለማሳካት፥ ክልላዊና አገር አቀፍ ከፍተኛ ደረጃ ያላቸው የሰላምና የዕርቅ ጥረቶች ተጀምረዋል።

በ2010 (እ.ኤ.አ. በ2018) የነበረው አገራዊ የለውጥ ሂደት በአገር አቀፍ ደረጃ 'የእርቅና ይቅርታ' ተስፋን ሰንቆ ነበር። ሆኖም ግን የፖለቲካ ልዩነቶችን ለመፍታት የሚያስችሉ ትክክለኛ ዘዴዎች በሌሉበት ሁኔታዎች ሂደቱ ብዙም ሳይቆይ በሁለቱም ጉዳዮች ላይ እንደ የፖለቲካ ቀመር መታየት ጀመረ። በርካቶች ማሻሻዮቹ የዜጎችን (በተለይ የሴቶችን) መብቶች ማስከበር እንዳልቻሉ በማሰብ፤ እንዲሁም በመላ አገሪቱ እየተፈጸሙ ያሉትን ሰፊ የሰብአዊ መብት ጥሰቶችን በማስከተል የማሻሻዮቹን ትክክለኛነት ጥያቄ ውስጥ ከትተዋል።[1]

እነዚህ ድክመቶች በሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች የሚመራ አገራዊ ምክክር ለውጥ ሂደቱ ጋር አብሮ እንዲጓዝ ጥሪ አቅርበዋል።[2] በ2011 (እ.ኤ.አ. በ2019) ዴስትኒ ኢትዮጵያ በሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች የሚመራ የውይይት ባህልን በፖለቲካ አውድ ውስጥ በማስፋፋት የተለያየ አመለካከት ያላቸውን የፖለቲካ እና የፖለቲካ ያልሆኑ ተዋናዮችን በአንድ ላይ ለማሰባሰብ ያለመ ሀገራዊ የውይይት መድረክ አስተዋውቋል። በዚሁ ሂደት ውስጥ ተሳታፊዎችን ለመለየት 'የብዝኃ መስፈርት ዳሰሳ' ተካሂዶ በጥቅምት ወር 2013 (እ.ኤ.አ. 2020) ሁሉን አቀፍ አገራዊ የምክክር ውጥን - ኢትዮጵያ (ማይንድ-ኢትዮጵያ) ተመስርቷል።[3] ሁሉን አቀፍ አገራዊ የምክክር ውጥን - ኢትዮጵያ በአገር ውስጥ ሴቶች የሚመሩ ድርጅቶችን እንደ አንድ የተለያ ፍላጎት ያላቸው የኅብረተሰብ ክፍል በመመልከት ተሳትፏቸውን ማረጋገጥ ላይ ያተኮረ አገር አቀፍ የምክክር መድረክ አዘጋጅቷል። በ2014 (እ.ኤ.አ. በ2021) ሁሉን አቀፍ ሀገራዊ የምክክር ውጥን - ኢትዮጵያ በሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን ተተክቶ፤ በየካቲት ወር 2015 (እ.ኤ.አ. በ2022) አገራዊ የምክክር ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጁ በሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ፀድቆ ሂደቱን እንዲመሩ 11 ኮሚሽነሮች ተሾሙ።[4]

ይህ አግባብ ባለው ተቋም ውስጥ የሰላም ጥረቶችን ከማጠናከር አንፃር እንደ አዎንታዊ እርምጃ ሊወሰድ ቢችልም፤ በአንዳንዶች ግን ጾታን ያማከለ፣ በጥናት ላይ የተመሰረተ እና ማኅበረሰቡን መሰረት ያደረገ የሰላም ሂደት ከመሆን ይልቅ ከፍተኛ የሆነ የፖለቲካ ጣልቃ ገብነትን ማበረታታት እንደሆነ ይታያል።[5]

# ሴቶች እና አገራዊ የምክክር ኮሚሽን፤ ድብልቁ ቦርሳ

አገራዊ የምክክር ኮሚሽን ሥርዓተ-ፆታን አካታች በመሆን ረገድ ስኬቶች ቢኖሩትመ፣ ለአንዳንድ ትችቶች ግን ተዳርጓል። በአዎንታዊ ጎኑ፣ በሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን አዋጅ ውስጥ የተቀመጠው የአካታችነት መርህ በኮሚሽነሮቹ በንቃት ተተግብሯል። ለዚህ ማሳያም ለሴቶች የተለየ ፍላጎቶች እንዳሏቸው የኅብረተሰብ ክፍሎች (ከ ዘጠኙ እንደ አንድ) እውቅና ከመሰጠት ባለፈ በሁሉም የተሳታፊዎች ስብስቦች ውስጥ ቢያንስ የ20 በመቶ ኮታ እንዲኖራቸው ተደርጓል። ከዚሁ ጎን ለጎን የሴቶች የፖለቲካ ፓርቲ አባላት የጋራ ምክር ቤት ሴቶችን በፖለቲካ መስመሩ ማካተት የሚያስችል አገራዊ አሰራር ለመንደፍ ጥረት አድርጓል። በተጨማሪም አገራዊ የምክክር ኮሚሽን

1 Ryan Lenora Brown, 'Autocrats' push for women in government: Window dressing, or real change?', *The Christian Science Monitor*, 5 February 2019, www.csmonitor.com/World/Africa/2019/0205/Autocrats-push-for-women-in-government-Window-dressing-or-real-change; Andinet Adinew Tesfaye and Endalkachew Abera Mekuriya, 'Conditions of Human Rights in Ethiopia in the Aftermath of Political Reform', *North Western Journal of Human Rights*, 19/1 (2020): 31–34.

2 Tegbaru Yared, 'Ethiopia's national dialogue: Reconciling competing approaches', Institute for Security Studies, 12–13, 2022.

3 ጥምረቱ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት፣ የሰላም ሚኒስቴር፣ ዴስቲኒ እና መሰል 'የሲቪል ማኅበረሰብ ድርጅቶች' እንደ ፍትህ ለሁሉም፣ ኢትዮጵያውያን ለሁሉ አቀፍ ውይይት፣ ኢኒሼቲቭ ፎር ቼንጅ የህሳብ መዓድን ያጠቃልላል።

4 'የኢትዮጵያ ሀገራዊ ምክክር ኮሚሽንን ለማቋቋም የወጣ አዋጅ፣ አዋጅ ቁጥር 1265/2021፣ የፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ፣ ታኅሣሥ 24 2014። የሀገራዊ ምክክር ኮሚሽንን ስራ ለመምራት አስራ አንድ መርሆች ተቀምጠዋል፣ ከእነዚህ ውስጥ የመጀመሪያው የሆነውን 'ማካተት' ነው።

5 ከዴስትኒ ኢትዮጵያ ተወካይ ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ, ሐምሌ 10፣ 2015

ከበርግሆፍ ፋውንዴሽን ጋር በመተባበር፤ እንዲሁም ከሁሉን አቀፍ አገራዊ የምክክር ውጥን - ኢትዮጵያ (ማይንድ-ኢትዮጵያ) የሚፈልጉትን የቴክኒክ ድጋፍ በማግኘት ከፍተኛ ደረጃ ላይ ባሉ ሴት ኃላፊዎች መካከል የአቅም ግንባታ ሥራ ለመስራት በጥረት ላይ ሲሆን፥ ይህም እስከ ታችኛው ታችኛው መዋቅር ድረስ ላሉ ሴቶች ይዳረሳል በሚል እምነት የሚሰራ ነው።

ነገር ግን በአራዊ የሠላም ግንባታ ሂደት ቅንጅት አለመኖሩ በተለይም የአካታችነት መርህን በማስከበር እና የኮታ ሥርዓት ተሳታፊዎች ምርጫ የፖለቲካ መጠቀሚያ በማድረግ ትችቶች ቀርበውበታል። በኋለኛው ጉዳይ፣ የአገራዊ ምክክር ኮሚሽን ክልላዊ የሕዝብ ተሳትፎ ስትራቴጂዎችና አካባቢያዊ ሂደቶች ሕጋዊነት እንዳያገኙ ገደብ ይፈጥራልም ይባላል ።[6] እነዚህ ጉድለቶች በከፊል የመነጩት ሴቶችን የማካተት ቀመር በክልላዊ ደረጃዎች የተስፋፋውን ማኅበራዊ፣ ባህላዊ እና መዋቅራዊ እንቅፋቶችን ለመፍታት ምንም ዓይነት የተቀናጀ ሙከራ ስላልተደረገበት ነው። ከዚህም በላይ፣ በአብዛኛዎቹ ጉዳዮች ላይ ሴቶች የሚመረጡት ሰፊውን የሰላም ሂደት ለማስቀጠል ወይም ሚናውን በአግባቡ ለመወጣት ባላቸው አቅም ተመዝነው ሳይሆን በፖለቲካዊ አቋሟቸው ላይ የተመሰረተ መሆኑን መረጃ ሰጪዎች ጠቁመዋል። በተመሳሳይ፣ ትርጉም ያለው አስተዋፅዖ ሊያበረክቱ የሚችሉ በተለይ በገጠር የሚኖሩ በርካታ ሴቶች ስለ ሂደቶቹ መረጃ የላቸውም። በመሆኑም በአገራዊ የምክክር ኮሚሽን የሚመራው ሂደት ክልላዊ ተሳትፎን ከአካባቢው ማኅበረሰቦች በመውሰድ በተቃዋሚ ፖለቲካ ፓርቲዎች መካከል ብቻ በማድረጉ ለሰላም፣ ለሰብአዊ መብቶችና ለአካባቢያዊ ስርዓት አስተዋፅዖ ሊያበረክቱ የሚችሉ ሴቶችን አግልሏል።

ከላይ እንደተገለፀው በአገር አቀፍ ደረጃ የሚዘጋጁ የሰላም ዕቅዶች በብሔራዊ ሆነ በክልላዊ ደረጃ አተገባበራቸው ግልጽነት ሲጎደለው ለአጠቃላይ ሂደቱ ሕጋዊነት እና ውጤታማነት ትልቅ አንድምታ ሊኖረው ይችላል። በዚህ ሁኔታ የተሳታፊዎችን ዓይነትና ብዛትን በተለይም በክልል ደረጃ የፖለቲካ ቀመር ማድረግ በሀገራዊ ምክክር ኮሚሽን የሚመራውን ሂደት በተሳትፎ ረገድ ሀገር-አቀፍ ተደርጎ እንዳይወሰድ ትልቅ እንቅፋት ይፈጥራል። በተለይም ሴቶችና ሌሎች ግፋዓን የማኅበረሰብ ክፍሎች ትርጉም ያለው ተሳትፎ እንዲያደርጉ ምቹ ከባቢ መፍጠርን በተመለከተ ከትብብር እና ከተቀናጀ አከባቢያዊ አሰራር አንፃር ግትር የሆነው ከላይ ወደታች ብቻ የሚወርድ አሠራር ተግባራዊነት ጥያቄ ውስጥ ይጥላል።

# ሰላም የማስፈን ሥራ በቤኒሻንጉል-ጉሙዝ

የኢትዮጵያ ቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል ከአስር አመታት በላይ በዘለቁና እርስ በርስ በተሳሰሩ የአመጽ እና የፀረ-አመጽ ውጊያዎች ውስጥ ሲዳክር ቆይቷል። ይህም በተፎካካሪ መንግስታዊ እና መንግስታዊ ባልሆኑ አካላት ውስብስብ ፍላጎቶች መሰረት የሚከወን ሲሆን፥ ከፍተኛ የሰብዓዊ መብቶች ጥሰት አስከትሏል። ከተቀሪው አገራዊ ሁኔታ በተመሳሳይ ከ2010 (እ.ኤ.አ. ከ2018) በኋላ ያለው ጊዜ በክልሉ ከፍተኛ ውጥረት በመኖሩ በርካታ ግድያዎች፣ የንብረት ውድመት እና የመዘዋወር ነፃነት እገዳዎች ታይተዋል።[7] በመሆኑም በ2014/2015 (እ.ኤ.አ. በ2021/2022) አገራዊ የምክክር ሂደት ከመጀመሩ ጎን ለጎን በክልሉ ያሉ ግጭቶችን ለመፍታት የተቀናጀ ጥረት ተደርጓል። ለዚህም ባህላዊ የሰላም ማስፈን ጥረቶችን ከመደበኛ የክልል ውይይቶች ጋር ማዋሃድ በዋነኝነት ይጠቀሳል።[8] እነዚህ መደበኛ ጥረቶች በክልሉ መንግስት እና በክልሉ ውስጥ በሚንቀሳቀሱ የተለያዩ ታጣቂ ቡድኖች መካከል በተደረጉ ተከታታይ የሰላም ስምምነቶች አማካይነት ቅርፅ ይዘዋል።[9] በአንፃራዊ መልኩ የግጭት መጠኑ ቢቀንስም በክልሉ ለተከሰቱት ሁከት መንስኤዎች በቂ መፍትሄ ባለማግኘቱ ተደጋጋሚ ግጭቶችና የሰብአዊ

6 ከሴቶች የፖለቲካ ፓርቲ አባላት የጋራ ምክር ቤት ተወካይ ጋር የተደረገ ቃለ መጠይቅ, ሐምሌ 17፣ 2015

7 Fekadu Adugna and Ketema Debale, 'Conflict and displacement in Ethiopia: the case of Benishangul Gumuz Regional State and Konso Zone, Southern Nations, Nationalities, and People's Region', EU Trust Fund for Africa (Horn of Africa Window) Research and Evidence Facility, January 2023, 24–25. https://blogs.soas.ac.uk/ref-hornresearch/files/2023/01/conflict-and-displacement-in-ethiopia.pdf; Ethiopian Peace Observatory, 'Metekel Conflict'. Accessed 26 July 2023, https://epo.acleddata.com/metekel-conflict/.

8 Fraol Bersissa, 'Analysis: Trials at peace in violence-ravaged Metekel', *Addis Standard*, 12 August 2022. Accessed 19 July 2023, https://addisstandard.com/analysis-trials-at-peace-in-the-violence-ravaged-metekel/.

9 'News: Benishangul Gumuz regional govt, rebel group sign peace agreement', *Addis Standard*, 19 October 2022, https://addisstandard.com/news-benishangul-gumuz-regional-govt-rebel-group-sign-peace-agreement/; 'News: Benishangul Gumuz region signs peace agreement with second rebel group, deal signed in Sudan', *Addis Standard*, 12 December 2022, https://addisstandard.com/news-benishangul-gumuz-region-signs-peace-agreement-with-second-rebel-group-deal-signed-in-sudan/.

መብት ጥሰቶች ቀጥለዋል።[10] ይህ መሳ የአካባቢው ነዋሪዎችን በተለይም ሴቶችን እና ልጃገረዶችን ለጉዳት ዳርጓል።[11]

በአጠቃላይ በማኅበራዊ እና ባህላዊ ምክንያቶች፣ የሴቶች ትርጉም ያለው ተሳትፎ በአብዛኛው በባህላዊ አውድ (እንደ ማኅበረሰብ ተፅእኖ ፈጣሪዎች) ብቻ ተገድቧል። በተመሳሳይ ወደ መደበኛ ጥረቶች ስንመጣ፣ ዘላቂነት ያለው የሰላም ሂደቱ የሚፈለገውን ያህል አካታች ስላልሆነ የሴቶች የፖለቲካ ተሳትፎ ብዙውን ጊዜ ከይስሙላነት ውክልና የዘለለ ተሳትፎ አልሆነም። በመሆኑም፣ የክልሉ ሴቶች በመደበኛ ሂደቶች ውስጥ ከመሳተፍ የተገለሉ ብቻ ሳይሆኑ ለሰብዓዊ መብቶች ጥሰት ተጋላጭ በመሆናቸው ለድርብርብ ችግሮች ተዳርገዋል። ከዚህም በላይ በባህላዊው የሰላም ግንባታ ሂደት የክልሉ ሴቶች ያበረከቱት አስተዋፅዖ በአብዛኛው እውቅና ሳይሰጠው ቆይቷል። የሴቶች ተሳትፎ በመደበኛ የሰላም ሂደቱ ውክልና ብቻ መገደቡ በአገራዊ ምክክር ኮሚሽን የሚመራው ሂደት ውስጥ የተዘረዘሩትን መሰናክሎች የሚያንፀባርቅ ነው። አካባቢያዊ፣ ማኅበራዊ እንዲሁም ባህላዊ ሁኔታዎችን ሙሉ በሙሉ ያገናዘበ፣ ሴቶችንና ሌሎች ግፋዓን ወገኖችን ሙሉ በሙሉ የሚያካትት እና በፖለቲካው ዘርፍ ጥቃትን የሚያስወግድ ክልል አቀፍ ሂደት እስካልተፈጠረ ድረስ የቤኒሻንጉል ጉሙዝ እንዲሁም በመላው አገሪቱ ያሉ ሴቶች መገለላቸው የማይቀር ነው። ይህም ለረጅም ጊዜ የሚቆዩ የሰላም ስምምነቶችን ዕውን የመሆን ዕድል ይቀንሳል።

# ማጠቃለያ

በዚህ አጭር ጥናት የተዳሰሱት ጉዳዮች እንደሚያሳዩት ሴቶችንና ሌሎች የተገለሉ ቡድኖችን ማካተት በኢትዮጵያ ውስጥ ዘላቂ የሰላም ሂደት እንዲሰፍን ቅድመ ሁኔታ ነው። በአገር አቀፍ ደረጃ፣ በሀገራዊ የምክክር ኮሚሽን መሪነት የተካሄደው የሰላም ሂደት አማካኝነት በተወሰኑ አካባቢዎች መሻሻሎች ቢታዩም የሴቶችን ትርጉም ያለው ተሳትፎ በየደረጃው ለማረጋገጥ ተጨማሪ ጥረት ማድረግ ያስፈልጋል። በቤኒሻንጉል ጉሙዝ ክልል የተከሰቱት ክስተቶች እንደሚያሳዩት የሴቶች ተሳትፎ መደበኛ ወዳልሆነ የሰላም ሂደት የሚያደላ ሲሆን፥ በመደበኛ ሂደት ውስጥ ለመሳተፍ ብቃት አላቸው ተብለው የሚታሰቡት ወንዶች ላይ ትኩረቱ ይጎላል።

ይህም ግጭትን ወደ ሰላም መቀየሪያ ሂደቶች ላይ - በተለይም በክልል ደረጃ - አካታችነትን ያማከሉ ንድፎችን እንደገና መንደፍ እንደሚያስፈልግ ያሳያል። እንደነዚህ ያሉ ሂደቶች እና ማኅበራዊ ቦታዎች ለነዋሪው ዘላቂ ሰላም ለማምጣት በተቻለ መጠን ከፖለቲካዊ ተፅዕኖ መላቀቅእና አካታች መሆን አለባቸው። ይህም በማስረጃ ላይ የተመሰረተና ማኅበረሰቡን ያማከለ ስልትን ስለሚጠይቅ በብዝኃ ዘርፍ ቅንጅት በመፍጠር፣ አመኔታን በመጠየቅ እና ህዝባዊ ህጋዊነትን በማግኘት ስኬታማ ስትራቴጂካዊ ውጤቶችን ማስመዝገብ ይቻላል። ለዚህም ከሁሉም የኅብረተሰብ ክፍሎች የተውጣጡ ሴቶች በመደበኛ ሂደቶች ሰላም ፈጣሪ ነን ብለው የይገባኛል ጥያቄ እንዲያነሱና ልማዳዊ አሰራሮችን ለመሞገት በሚደረገው የቅስቀሳ ሥራ ላይ መደገፍ አለባቸው።

10 ACAPS, 'Ethiopia: Humanitarian situation in Guba woreda, Benishangul Gumuz', Thematic Report, 30 June 2023, 2. https://reliefweb.int/report/ethiopia/acaps-thematic-report-ethiopia-humanitarian-situation-guba-woreda-benishangul-gumuz-30-june-2023#:~:text=Humanitarian%20presence%20and%20response%20capacity,of%20restrictions%20in%20the%20woreda.

11 በሐምሌ፣ 2015 የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባኤ ባወጣው መግለጫ በክልሉ ከተፈናቀሉት 469,609 ሰዎች መካከል 77,975ቱ ከአምስት አመት በታች ያሉ ህፃናት ሲሆኑ 20,135ቱ የሚያጠቡ ወይም ነፍሰ ጡር እናቶች መሆናቸውን ገልጿል።. ይመልከቱ፡ የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ጉባኤ፣ 'ታጣቂ ቡድኖች የሚሰነዝሩ ጥቃቶች መቆም አለባቸው'፣ አስቸኳይ ጋዜጣዊ መግለጫ፣ ሐምሌ 5 2015።